# ወንጀል የለወጠው

ከዳንኤል በቃሉ

አንዲት ፊልም አይቼ፣ ድረ-ገጽ ያወጣው፣
አዲሱ ሰባኪ፣ ወንጀል የለወጠው፣
በግራ ቀኝ ጉንጩ፤ እንባውን ለቀቀው፤
በከሃዲነቱ፣ ማንንም ሳይፈራ፣
በኢትዮጵያ ላይ፣ ላመጣው መከራ፣
ንሥሃ መግባቱን፣ ጥፋቱን አወራ፣
እንደው በድፍንፍን፣ ቅንጣት ሳያብራራ።

ጠሩን እየመራ፣ እንዳልተታኮሰ፣
በሥልጣን ብልግና፣ እንዳልተከሰሰ
ከስር ቤት ሲያስገቡት፣ ስኳር እየላሰ፣
ሁሉንም ረስቶ፣ አምርሮ አለቀሰ፣
ምን ያለው ጊዜ ነው፣ የተልከሰከሰ?!
ታምራት ለዓይኔ፣ የተወናበደ፣
በቃሊቲ እስር ቤት፣ ዳግም ተወለደ (born again)
አሁን የት የገኛል፣ እንዴ ጴንጤ ጀግና፣
ሁለተኛውን ሰው፣ ማራኪ በመና።

ጌታ ኢየሱስን፣ ያልተቀበላችሁ፣
አሁን ተቀበሉት፣ አለ ከፊታችሁ፣
ለእኔ የሰጠውን፣ በረከት ይስጣቸሁ፤
እያለ ሰበከ፣ እያስጨበጨበ፣
አዲሱ ሰባኪ፣ በእንባ የታጠበ።

የወንጌል ምርኮኛው፣ ያ የጡሩ መሪ፣
አልቅሱ አትፈሩ፣ አልቅሽ አትፈሪ!
እንኳንስ ሰውና፣ አልቅሷል ፈጣሪ፣
እያለ ሰበከ፤ ደህና ሰንብች ሱሪ።

ለካስ “ዴሞክራሲ”፣ ውጤቱ ይኸ ነው፣
መለሰ ዜናዊ፣ ነፍስህን አይማረው።
ከቶ ምን ይል ይሆን፣ የኢሕዴግ ጎራ፣
ታምራት ምልምሉ፣ እንደዚያ ሲያጓራ?

ለየለት ታምራት፣ በመዝሙር አበደ፣
እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ሶስት ጊዜ ካደ፤
በፊት ጃንሆይን፣ ቀጥሎም ኢሕአፓን፣
አሁን ኢሕአዴግን፣ ጥላ ከለላውን፣
የእምነቱን ይሆን፣ ወይም የፍራቱን፣
ዛሬም አለቀሰ፣ አፈሰሰ እንባውን።
ፊልሙን ሲያስተውሉት፣ ይህ ነገር ይገርማል፣
“መሸጥ የለመደ፣ እናቱን ያስማማል።”
የዚህ ሰው በሽታ፣ በጣም ያሳዝናል፣
የነገሥ ሕይወቱ፣ ምን ያስተማምናል?

እባክህ ፈጣሪ፣ ሌላ ጉድ ሳንሰማ፣
መለሰን ገላግለን፣ ልባችን አይድማ!
ለዚህን በቅተዋል፣ እነአባ ባድማ?!
የጀግና ህዝብ ታሪክ፣ እንደምን ይግማማ?